ጠላት ያዩአቸው ስለነበር ደስ ሳይላቸው አልቀረም። በሰሜኑ የደረሰው ወረራ ለደቡብም አልቀረለትም። በ586 ከክርስቶስ ልደት በፊት ባቢሎናውያን በናቡከደነጾር መሪነት መጥተው ኢየሩሳሌምን አጠፉ። ቤተመቅደስንም አፈረሱ፤ ሕዝቡንም ማርከው ወሰዱ።

## ማጠቃለያ

በዚህ ዘመን በደብተራ ኦሪት የነበረችው ታቦተ ጽዮን ወደ ቤተ መቅደስ ገባች። እንዲሁም ዛሬ ላለው የቤተክርስቲያን አሠራር መሠረት የጣለ ዘመን ነበር። ንጉሡ ዳዊትም በሰሞን የተመደቡ / ሰሞኝ ካህናት/ ካህናትና መዘምራንን፣ ሰሞነኞችን፣ ለቤተ መቅደስ በመመደብ ዛሬ ለምንጠቀምበት ሥርዓት መሠረቱን አስቀምጧል። ሌላው ይህን ዘመን ልዩ የሚያደርገው በንጉሥ ሰሎሞን ዘመነ መንግሥት ታቦተ ጽዮን ወደ ኢትዮጵያ መምጣቷ ነው።

እስራኤላውያን ለሁለት ከተከፈሉ በኋላ በይሁዳና በእስራኤል የነገሡ ነገሥታትና በዘመናቸው የነበሩ ነብያት እንዲሁም በጊዜው የነበሩ ሌሎች መንግሥታት የሚከተሉት ናቸው።

**በይሁዳና በእስራኤል የነገሡት ነገሥታትን በዘመኑ የነበሩት የነቢያት ዝርዝር ሰንጠረዥ በገጽ 258 ይመልከቱ**

## ምዕራፍ አራት

**ይህ ዘመን የአይሁድ ንጉሥ ሴዴቅያስ በባቢሎን ምርኮ ከሞተ በኋላ /2ኛ ዜና. 36÷1-16/ ያለውን ጊዜ በተለይ ይመለከታል። ይህም ከ586 ከክርስቶስ ልደት በፊት እስከ ክርስቶስ መወለድ ያለው ጊዜ ነው። ይህም 4914-5500 ዓመተ ዓለም ነው።**

**ነቢያት፡- በአጠቃላይ እውነተኞችና ሐሰተኞች ተብለው በሁለት ሲከፈሉ በቅዱሳት መጻሕፍት የምናገኛቸውና ከእውነተኛ አምላክ ከእግዚአብሔር የሆኑትን ነቢያት የቃል እና የጽሑፍ ብለን እንለያቸዋለን።**

- **የጽሑፍ ነቢያት በማዕረጋቸው /በብቃታቸው/ ዐበይትና ደቂቅ ይባላሉ።**
- **የመጀመሪያው የብሉይ ኪዳን ነቢይ አዳም፤ የመጨረሻው መጥምቀ**
- **መለኮት ቅዱስ ዮሐንስ፤ ሊቀ ነቢያት ደግሞ ነቢይና መስፍን የነበረው ሙሴ ነው።**

**ካህናት፡- ክህነት ተክህነ፣ አገለገለ፣ ተሾመ ከሚለው ግስ የተገኘ ሲሆን ትርጉሙም ሹመት፣ አገልግሎት፣ በተቀበሉት ሥልጣን መሥራት ወይም አገልግሎት መፈጸም ይሆናል።**

- የክህነት አጀማመሩን ስንመለከት ከመጀመሪያው ሰው ከአዳም ጀምሮ እንደሆነ እንገነዘባለን:: እግዚአብሔር አዳምን ነብይ፣ ካህን አድርጐ ሾሞታል:: ከእርሱ በኋላ እስከ ሙሴ ያሉ አበው በበረከተ አበው እየተሾሙ ትንቢትና ክህነትን ገንዘብ አድርገዋል::
- እግዚአብሔር ፈቅዶ በሕግ ሙሴን፣ አሮንና ልጆቹ እንዲካኑ /ካህናት/ እንዲሆኑ አዘዘው:: ዘጸ.28÷40፣ 29÷46 /እንዲሁ ተፈጸመ/ ዘሌ. 8÷1::
- ሳይሰጣቸው የክህነትን አልግሎት ለመፈጸም የተነሱ ሰዎች ተቀጥተ ዋል:: ዘኍ.16÷1-35፣ 2ኛ ዜና. 26÷18-20::

ከዚህ በላይ የተመለከተው በብሉይ ኪዳን ስለነበሩት ነቢያትና ካህናት አገልግሎት ምርጫ ለመግቢያ ያህል ጠቅለል ባለ መልኩ ሲሆን፣ ወደ ተነሳንበት ዘመን ስንመለስ አይሁድ እግዚአብሔር ነቢያቱን እየላከ ዕ ለት ዕለት ቢመክራቸውም፣ ቢያስተምራቸውም ልቦናቸውን አደንድነው አልተመለሱም፤ የእልከኝነታቸውም ውጤት ጥፋት ሆነ:: የባቢሎን ንጉሥ ናቡከደነጾር ኢየሩሳሌምን በብዙ ሠራዊት ከበባት፣ ሕዝቡንም በሠይፍ ገደላቸው:: የቤተመቅደሱን ንዋያተ ቅድሳት ሌሎችንም ወስዶ ቤተ መቅደሱንና ቅዱሳት መጻሕፍቱን አቃጠለ:: ከግድያ የቀሩትንም ማ ረካቸው:: ወስዶም ለንጉሡና ልጆቹ ባሪያዎች አደረጋቸው:: እግዚአብሔ ር ያልተናገረውን አያደርግም፤ የማያደርገውንም አይናገርም፤ የተናገ ረውንም አያስቀርምና በነቢያቱ ይልቁንም በኤርምያስ አፍ እንደተናገረው ሆነባቸው:: 2ኛ ዜና. 3611-21፣ ኤር. 39÷1-10::

በባቢሎን ተማርከው እያሉም ወገኖቹ ፈጽመው ይከፉ ዘንድ የማይወድ እግዚአብሔር እንዲሁ አልተዋቸውም:: በቅዱሳን ነቢያት አማካኝነት ተስፋ ይሰጣቸው ነበር:: ከእነዚህም ተማርከው ከተወሰዱት ሕዝቅኤል፣ ዳንኤል፣ ሠለስቱ ደቂቅ፣ እዚያው የተወለዱ ዕዝራ፣ ሐጌ፣ ዘካርያስ፣ ዘሩባቤል /ንጉሥ / ኢያሱ - ካህን ይገኙበታል::

መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚገልጽልን እግዚአብሔር ምርጦቹ ቅዱሳንን ክብርና ሞገስ ሰጥቶ በአሕዛብ ፊት አከበራቸው:: በተለያዩ ተአምራትም የእስራኤል አምላክ እሱ እግዚአብሔር መሆኑን ጣኦታትም አማልክት እንዳይደሉ ገለጠ::

በሰማይ መላእክት /ዘካ. 1÷12-17፣ በምድር ቅዱሳን ያቀረቡትን የምልጃ ጸሎት/ ዳን.9÷3-27/ እና የእስራኤልን መጸጸት /መመለስ/ ተ መልክቶ እግዚአብሔር «ወደ ኢየሩሳሌም በምሕህረት ተመልሻለሁ፤ ቤቴ ይሠራበታል» አለ:: ከእግዚአብሔር ከታረቁ ሁሉም ይታረቃልና

እግዚአብሔር የፋርስን ንጉሥ ቂሮስንና ሌሎችንም አስነስቶ በአዋጅ ቤተ መቅደስ ታነጸ፣ በምርኮ የነበሩት ተመለሱ፣ የኢየሩሳሌም ቅጽር ተ ሠራ:: /ዕዝ.1÷1-14/ ከባቢሎን ምርኮ በኋላ ብዙ እስራኤላውያን ወደ አገራቸው አልተመለሱም:: ስለዚህም በየአገሩ ምኩራብ እየሠሩ ሃይማኖታቸውን ጠብቀው በዝርወት ይኖሩ ነበር::

ወደ ሀገራቸው የተመለሱትም ቢሆኑ በነጻነት አልኖሩም:: በተለያዩ ጊዜያት፣ በተለያዩ ቅኝ ገዥዎች ይያዙ ነበር:: ከ70 ዓመት ምርኮ በኋላ ጥቂት እንደቆዩ በፋርስ ተወረሩ:: አሁንም እንደገና በ330 ቅድመ ልደተ ክርስቶስ ጀምሮ በሮማውያን ቅኝ ግዛት ሥር ከሆኑ በኋላ ሥርዓታቸው፣ አኗኗራቸው፣ ባህላቸው፣ አስተዳደራቸው እጅጉን ተለውጦ ነበር::

በዚህ ዘመን ከተነሡት የመቃቢስ ልጆች መቃብያን ይገኙበታል:: መጽ.መቃብያንና ሌሎችም የቤተክርስቲያን መጻሕፍት እንደሚገልጹት መቃብያን ስለ ሃይማኖታቸውና ስለ አገራቸው ብዙ ተጋድለዋል:: ብዙ መከራም ተቀብለዋል:: ትንሣኤ ሙታን የለም ይሉ ለነበሩ መናፍቃን /ሰዱቃውያንም/ መልስ ሰጥተዋል:: ሊቀ ካህናት አዛርያስ ከነቤተሰቡ ስለሃይማኖቱ ሰማዕትነት የተቀበሉትም በዚህ ዘመን ነበር:: በአጠቃላይ ነቢያትና ካህናት በምርኮ ሳሉም ከዚያም ጊዜ በኋላ ሕዝቡን ይመክሩ ከእግዚአብሔር ጋር ያስታርቁ፣ መስዋዕት በማቅረብ ያገለግሉ ነበር:: ስለ ዘመነ ሐዲስም ለቤተክርስቲያን ምሳሌ፣ በትንቢት፣ በሱባዔ ቆጥረው ተስፋ ድኅነትን እየተመለከቱ ይጠብቁም ነበር:: በዚህ መልኩ አዳምን ከሲኦል ባርነት፣ ከዲያብሎስ ቁራኝነት ነፃ አወጣለሁ ሲል ልዑል ባህርይ እግዚአብሔር የቀጠራት ጊዜ 5500 ዘመን እየደረሰች ነበር:: ገላ. 4÷4::